# የፕሮጀክት የጽንሰ-ሀሳብና የፕሮጀክት ዕቅድ ሰነድ ለማቅረብ የወጣ ጥሪ

አነስተኛ የገንዘብ ድጋፍ መስጫ ተቋም Small Grants Programme (SGP) በዓለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ የገንዘብ ተቋም Global Environment Facility (GEF) የገንዘብ ድጋፍ በመታገዝ በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም United Nations Development Program (UNDP) አማካኝነት የሚተገበር ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ. በ1992 ዓ.ም. ሥራውን የጀመረው ይህ ፕሮግራም፣ ህጋዊ ዕውቅና ያላቸውን የማሕበረሰብ ድርጅቶች Community Based Organizations (CBOs) እና ሀገር በቀል የሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን Non-governmental Organizations (NGOs) እንቅስቃሴ በገንዘብ ያግዛል፡፡ ይህ የገንዘብ ድጋፍ በዋናነት የመሬት ክለትን መከላከል (Prevention of Land Degradation)፣ የብዝሐ-ህይወት ጥበቃ (Conservation of Biological Diversity)፣ አሉታዊ የአየር ንብረት ለውጦችን ለመመከት (Abatement of Climate Change)፣ International Waters እና Chemicals ላይ የሚሰሩ ሥራዎችን ለመተግበር የተቀረፀ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከላይ የተዘረዘሩት ሥራዎች የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎችን ኑሮ እንዴት ማሻሻል እንደሚችሉ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት መስኮች ዙሪያ ፕሮጀክቶችን ለማከናወን የሚፈልጉ የማሕበረሰብ ድርጅቶች እና ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተዘጋጀውን የሰነድ ማቅረቢያ መመሪያ በመከተል አጠር ያለ የፅንሰ-ሐሳብ ሰነድ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ጥሪ ያደርጋል፡፡

**<u>አመልካቾች የፅንሰ-ሐሳብ ሰነድ ከማስገባታቸው በፊት የገንዘብ ድጋፍ ሊሰጥባቸው ስለተወሰኑት ቦታዎች (Land/ waterscape) ከታች በተመለከተው አድራሻ በቅድሚያ መረጃ ማግኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡</u>**

የፅንሰ-ሐሳብ ሰነዳቸው ተቀባይነትን ያገኙ አመልካቾች በሚሰጣቸው አስተያየት እና የጊዜ ገደብ መሠረት የተሟላ የፕሮጀክት ዕቅድ ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የማመልከቻ መመሪያዎች፣ የፅንሰ ሀሳብ እና የፕሮጀክት ዕቅድ ሰነድ እንዲሁም ስትራቴጂክ ዶክመንቶችን ከዚህ በታች በተመለከተው አድራሻ ማግኘት ይቻላል፡፡

**የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ሕንፃ**
**አንደኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር** 109B
**ቂርቆስ ክፍለ-ከተማ ቀበሌ** 7
**የመ.ሣ.ቁጥር** 5580
**አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ**
**የስልክ ቁጥር:** +251 11 5-540964/66
**የፋክስ ቁጥር:** +251 11 5-540963
**ኢ-ሜይል:** **zeleke.tesfaye@undp.org** or
**feleke.bebzha@undp.org**